# ምነዉ በስተእርጅና ጣሪያ ላይ?

**ከብርሃኑ ወልደሰንበት**
**ከሰሜን አሜሪካ**

አቶ አሰፋ ጫቦ በፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ላይ ያቀረቡትን ፅሁፍ ሳነብ ሰራዊት ፍቅሬና ሙሉአለም ታደሰ ለዲኤች ገዳ ቆርቆሮ ማስታወቂያ - ምነዉ በስተእርጅና ጣሪያ ላይ? በሚል ርእስ የሰሩት ድራማ ትዝ አለኝ! እንደ አጋጣሚ ሆኖ ፕሮፌሰር በየነን ለ 24 ዓመታት በቅርብ አውቃለሁ፡፡ እንዲሁም አቶ አሰፋ ጫቦን ለረጅም ዓመታት በድንቅ ጽሁፍቹ አውቃለሁ፡፡ የ 15 ፖለቲካ ድርጅቶች በፈረንጆች አቆጣጠር 2003 ህብረት ምስረታ የጉባኤ አባል ሆኜ ሰሜን አሜሪካ እንደመጣሁ ጉባኤ እንዳበቃ አቶ አሰፋ ጫቦ ዋሽንግተን ዲሲ መጥቶ የደቡብ ልጆችን እፈልጋለሁ ብሎ ፕሮፌሰር በየነ በሌለበት አሰባስቦን ዱከም ሆቴል በራስ አገዝ እራት ውይይት አደረግን፡፡ በየነ በህብረቱ የበላይ መሪነት በመመረጡ አለመደሰቱን አሳውቆን ተለያየን፡፡

እኛም ታዝበነው ዝም አልን፡፡ ስለ ትውውቁ ይህን ያህል ካልኩኝ ወደ ያነበብኩት ፅሁፍ ስመለስ ሰዎች ሲያረጁ እንደ ህጻን ያረጋቸዋል የሚለው ታወሰኝ፡፡ መቼም ሰውን ማወቅን የመሰለ ከባድ ነገር የለምና በዚህም ምክንያት መናገር እንጂ መፃፍ የማልወደውን ብእር እንዳነሳ አድርጎኛል፡፡ 'የዘር ንግስና በመድረክም ላይ' ከሚለው የአቶ አሰፋ ሃሳብ ስነሳ በአንድ ወቅት ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ ሃዲያዎች የኢህአዴግን ውስብስብ ሴራ በጣጥሰው ፕሮፌሰር በየነንና ሎሌች ታጋዮችን በፓርላማ አባልነት ከመረጡ በኋላ የእኛ መሪ እኮ ግርማ ሞገሱ ለሃገር መሪነትም ይበቃል ብለው እንደነበር ሰምቶ ኖሮ በአንድ ወቅት ፓርላማ ላይ ፕሮፌሰር በየነ በማያላውስ እውነተኛ ሃሳብ ሲያጣድፈው "እኔ እኮ በአፍንጫዬና በፀጉሬ አልተመረጥኩም" ያለውን ያስታውሰኛል፡፡ አቶ አሰፋ ባይኖር ኖሮ እኔ ፖለቲካ ውስጥ እንደምገባ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡

1983 ዓ.ም ሽግግር መንግስት ሲመሰረት ከበረሃ የመጡት ከነኮፍያቸውና ሲጋራቸው፣ የድል አጥቢያ አንበሳዎችና "እኛም ደርግን አንወድም" የሚሉ በበኩላቸው ካፖርታቸውን ለብሰው እንዲሁም እንደባለቤቶቹ ለመሆን ትግርኛ የሚቃጣቸው "አተአ ዋ" የሚሉ ሁሉ አጋጥመውኛል፡፡ ወደ ቁም ነገሩ ስመለስ አቶ አሰፋ ጫቦም ኢህአዴግን መንገድ ላይ ሳይሆን ከተማ ከገቡ በኋላ ተቀላቅሎ ግማሹን ደቡብ "ኦሞቲክ ህዝብ" በማለት ጋሞ ከጎፋን፣ የቀድሞን ከፋ ክፍንለሀገርን ሽኬቾን ጨምሮ "የኦሞቲክ ህዝብ ተጠሪ እኔ ነኝ" በማለት ወንበር አገኝቶ ፓርላማ ገባ፡፡

ይህንን ሁኔታ ሁሉም ማንነቱንና ታሪኩን የሚያውቅ ከየአቅጣጫው ተጠራርቶ፣ የከፋ አካባቢ ህዝቦች የራሳቸው የሆነ ታሪክና ንግስና የነበራቸው መሆኑን በመግለፅ፣ ማመልከቻ ለሽግግር መንግስቱ በመፃፍ ሁለት ወንበር በሽግግሩ ፓርላማ ተመደበላቸው፡፡ በዚህም ፊ/ታ ዘውዴ ኦቶርና ዶር አሸናፊ ማሞን ወከለን ላክን፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ በፓርላማ የነበሩ የደቡብ ህዝቦች ተወካዮች መከረው መጋቢት 2 ቀን 1984 ዓ.ም ደቡብ ህብረትን መሰረቱ፣ መስራች ጉባኤውም ላይ ነበርኩ። በዚያ ወቅት አቶ አሰፋ ጫቦ አልነበረም ፡፡

ስለሆነም ከዚያ በፊት ያልነበረውን "ደቡብ ህብረት መሰረትኩ፣ ሊቀ መንበርም ነበርኩ" የሚለው ወሬ ከወዴት የተፈጠረ እንደሆነ ግራ የሚያጋባ ነው! ከሀምሌ 1983 ቱ የሽግግር መንግስት ምስረታ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ከኢህአዴጎች ጋር በስልጣን ጉጉት ነው መሰለኝ ከመወዛገቡ የተነሳ ሃገር ጥሎ ወደ ውጭ መውጣቱንና በዚያው መቅረቱን ነበር የደቡብ ህብረት ታጋዮች የምና ውቀው። ስለዚህ ወደዚህ ሽሽተን ከመጣነው እዚያው ሀገር ቤት ከአገዛዙ ጋር መከራቸውን የሚያዩት ጀግኖች ናቸው።

በአንድ ወቅት እኔ በምኖርበት በላስ ቬጋስ ከተማ የመድረክ አመራር አባላት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና ኢንጂኔር ግዛቸው ሰብስበውን ስያወያዩን አንድ በሰላማዊ ትግል የማያምን ይመስለኛል "እናንተ ነፃነት ከሌላችሁ ድርጅት ምን ያደርጋል አትተዉትም?" ይላቸዋል። በሁኔታው የተገረሙት ዶ/ር ነጋሶ ሲመልሱ "ታድያ እጃችንን አጣጥፈን ቁጭ እንበል ወይስ እንደናንተ ሽሽተን ከሀገር እንውጣ?" ያሉት ትዝ ይለኛል። በእርግጥ በተቃውሞ ፖለቲካ መሪነት ፕ/ር በየነ ለመሪነት ተደጋግሞ ይመረጣል። ያ የሚሆነው ህዝባችን በእርሱ ላይ ባለው እምነት ምክንያት ኃላፊነት ይሰጠው እንደሆነ እንጂ እርሱ መመረጥ በመፈለግ ሌሎችን አስገድዶ እንዳልሆነ ይታወቃል። ሀገር ቤት ያሉትም ታጋዮች ለትግሉ የሚመቻቸውን ሰው የሚመርጡ ይመስለኛል።

ሌላው መሪያችን መሆን ያለበት ሁሉ እንደብቃቱ ለትግሉ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ መጠበቅ እንጂ "ተተኪ አመራር" እያሉ የኢህአዴግን የማጭበርበሪያ መፈክር እንደማይክሮፎን ማስተጋባት ለትግላችን ጠቃሚ አይደለም። ለዚያውም ቢሆን አገዛዙ ተተኪዎች መሆን የሚችሉትን እየተከታተለ ያስራል፣ ይገድላል፣ ያሳድዳል። ለአብነት ያህል ብርቅዬ ተተኪ ሊሆኑ የሚችሉት እንደነ

አንዱ አለም አራጌ፣ ሀብታሙ አያሌው፣ በቀለ ገርባና አብርሃ ደስታ የት እንዳሉ መጥቀስ ይበቃል።

በተጨማሪ ስላለመታሰራቸው ከሆነ እነ ዶ/ር መረራ፣ ፐ/ር በየነ እና ሌሎችም መታሰር ለስርዓቱ ሊያስከትል የሚችለውን የፖለቲካ ኪሳራ በመገንዘብ እንጂ ለነርሱ በማዘን አይደለም። የስርዓቱን ሸፍጥ ለተረዳ ሰው የነኝህ ታጋዮች ያለመታሰር ግልጽ ነው። የፀረ ሽብር ህጉ ዘንግቶአቸው አይደለም። አቶ አሰፋ ጫቦ በፐ/ር በየነ "ሸፍጠኛ" እንደሆነ ለመግለጽ ሞክረዋል።

ነገር ግን አብሬው ለአመታት እንደመታገሌ ፐ/ር በየነን እኔ እንደማውቀው ለሀገሩና ለህዝቡ ታማኝ፣ ሩህሩህ፣ በራስ የሚተማመን እና የማሳመን ብቃት ያለው እንጂ ሸፍጠኛ ተብሎ የሚዘለፍ ሰው ሊሆን አይችልም። ለሀገር መሪነት ሙሉ ብቃት ያለው ሙሁር ነው። ስለዚህ ሊጋሽ አሰፋ የምመክረው እርስ በእርስ አለመተማመንን አስወግደን የጋራ ጠንቃችንን በጋራ ቀይረን በውድ ሀገራችን ሞታችንም ሆነ ሁለንተናዊ ክብራችን ቢሆን እንደሚመረጥ ነው።

ዋናው ፍሬ ነገር ሲጠቃለል እንደ ፐ/ር በየነ ያሉት መስዋ ዕትነት በመክፈል ምኞትን ትተው ለዴሞክራሲና ለሀገር አንድነት የሚታገሉትን በውሸት ለማጥቆር መሞከር የኋላቀር አሮጌ የፖለቲካ ስልት ከመሆን አይዘልቅም።

ፍትህና ነፃነት ለሀገራችን ህዝብ!

ብርሃኑ ወልደሰንበት ኬቶ Email - akobre@yahoo.com